# ሲኖዶስ

2014
2016

## ለሲኖዶሳዊት ቤተ ክርስቲያን

ኅብሮነት / ተሳትፎ / ተልእኮ

# የዝግጅት ሰነድ

SYNODUS EPISCOPORUM

SYNOD OF BISHOPS

## መውጫ


1. የአብሮነት ጉዞ ጥሪ
2. ሲኖዶሳዊ አቋም ያላት ቤተ ክርስቲያን
3. ቅዱሳት መጻሕፍትን ማዳመጥ
   ኢየሱስ፣ ሕዝብ፣ ደቀ መዛሙርት
   የለውጥ እጥፍ ኃይል፡- ጴጥሮስና ቆርኔሌዎስ (የሐዋ. ሥራ 10)
4. ሲኖዶሳዊነት በተግባር፡- ሕዝበ እግዚአብሔርን ማማከሪያ መንገዶች
   መሠረታዊ ጥያቄ
   የሲኖዶሳዊነት ልዩ ልዩ መገለጫዎች
   መዳሰስ የሚገባቸው አስር ቁልፍ ርእሰ ጉዳዮች
   1. አብሮ ተጓዦች
   2. ማዳመጥ
   3. መናገር
   4. ማክበር
   5. በተልእኮ ውስጥ የጋራ ኃላፊነት
   6. ውይይት በቤተ ክርስቲያንና በህብረተ ሰብ ዘንድ
   7. ከሌሎች ክርስቲያን ቤተ እምነቶች ጋር
   8. ሥልጣንና ተሳትፎ
   9. ማስተዋልና መወሰን
   10. በሲኖዶሳዊነት ራሳችንን ማነጽ ለምክክሩ አስተዋጽኦ ማድረግ



## አኅጽሮተ ቃላት

| | |
|---|---|
| ITC | INTERNATIONAL THEOLOGICAL COMMISSION |
| DV | VATICAN COUNCIL II, Dogm. Const. Dei Verbum (18 November 1965) |
| EC | FRANCIS, Ap. Const. Episcopalis communio (15 September 2018) |
| EG | FRANCIS, Ap. Exhort. Evangelii gaudium (24 November 2013) |
| FT | FRANCIS, Enc. Lett. Fratelli tutti (3 October 2020) |
| LG | VATICAN COUNCIL II, Dogm. Const. Lumen gentium (21 November 1964) |
| LS | FRANCIS, Enc. Lett. Laudato si' (24 May 2015) |
| UR | VATICAN COUNCIL II, Decree Unitatis redintegratio (21 November 1964) |

# ለሲኖዶሳዊት ቤተ ክርስቲያን:
# ኅብሮነት፣ ተሳትፎ እና ተልእኮ

1. የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ለሲኖዶስ ተጠርታለች። «ለሲኖዶሳዊት ቤተክርስቲያን፡-ሱታፌ፣ ተሳትፎና ተልእኮ» የተሰኘው ጉዞ እ.አ.አ. ከጥቅምት 9-10፣ 2021 በሮም፣ እ.አ.አ. ጥቅምት 17፣ 2021 በእያንዳንዱ ልዩ ቤተክርስቲያን በደማቅ ክብረ በዓል ይጀመራል። (1) ከእነዚህ መሠረታዊ ደረጃዎች አንዱ 16ኛው የጳጳሳት መደበኛ ሲኖዶስ እ.አ.አ. ጥቅምት 2023 የሚካሄድ መሆኑ ሲሆን ፣ የሚቀጥለው የክንውን ምዕራፍ የልዩ አብያተ ክርስቲያናትን ተሳትፎ የሚጠይቅ ይሆናል። (ንጽ. EC, አንቀጽ 19-21)። በዚህ ሶኖዶስ ላይ፣ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንሲስኮስ ኩላዊት ቤተክርስቲያን ለህልውናዋና ለተልእኮዋ ወሳኝ በሆነው ርእሰ ጉዳይ ላይ እንድታስተነትን ጥሪ ያቀርባሉ። «እግዚአብሔር በሶስተኛው ሺህ ክፍለ ዘመን ከቤተክርስቲያን የሚጠብቀው የሲኖዶሳዊነት ጉዞ ይህ ነውና።» ይህ ከሁለተኛው የቫቲካን ጉባኤ «የተሐድሶ» ጥሪ ቀጥሎ የመጣው ጉዞ በራሱ ጸጋም ግዴታም ነው። ቤተክርስቲያን በአንድነት

[1] የሲኖዶሱ የጉዞ ምዕራፎች ተዘርዝረዋል



በመጓዝና የተጓዘችበትንም መንገድ በጋራ በማሰላሰል፣ ከተሞክሮዋ በሱታፌ መኖርን፣ ተሳትፎዋን ማጠናከርን፣ ራስዋን ለተልእኮ ማዘጋጀትን ትማርበታለች። በመሠረቱ፣ ‹‹የአብሮነት ጉዞአችን›› ቤተክርስቲያን መንፈሳዊ ተጓዥና የእግዚአብሔር ልኡክ ሕዝብ የመሆንዋን ባህርይ በሚገባ ገቢራዊ ያደርጋል፣ ይገልጻል።

## . . . this path of synodality which God expects of the Church of the third millennium . . .

2. በዚህ ረገድ መንፈሳችንን የሚያነቃቃውና የሚመራን አንድ መሠረታዊ ጥያቄ አለ፤ እርሱም፣ ዛሬ ከአጥቢያ አንሥቶ እስከ ዓለም አቀፍ ደረጃ ድረስ በተለያዩ እርከኖች የሚካሄደው ይህ ‹‹የአብሮነት ጉዞ›› ቤተክርስቲያንን በተሰጣት ተልእኮ መሠረት ወንጌልን እንድትሰብክ ሊረዳት የሚችለው እንዴት ነው? መንፈስ ቅዱስስ ሲኖዶሳዊት ቤተ ክርስቲያን ታድግ ዘንድ ምን እርምጃ እንድንወስድ ይጠራናል? የሚል ነው።

ለዚህ ጥያቄ በጋራ ምላሽ ለመስጠት፣ እንደ ነፋስ ‹‹ ወደፈለገበት የሚነፍሰውን፣ ድምፁን ብትሰሙም፣ ነገር ግን ከየት እንደሚመጣና ወዴት እንደሚሄድ የማታውቁትን›› (ዮሐ. 3፡ 8) መንፈስ ቅዱስን ለመስማት፣ እርሱም በመንገዳችን ላይ ያዘጋጀልንን ድንቅ ነገር ለማየት ዝግጁ መሆንን ይጠይቃል። ስለዚህ፣ በሂደት እያደገ ከሚሄደው ከሲኖዶሳዊ የለውጥ ፍሬዎች



[2] ፍራንሲስኮስ፣ የጳጳሳት ሲኖዶስ የተመሠረተበት 50ኛ ዓመት መታሰቢያ ክብረ በዓል በማስመልከት ያደረጉት ንግግር፣ (እ.አ.አ. ጥቅምት 17 ቀን 2015)



አንዳንዶቹን መቋደስ እንድንጀምር የሚረዳን እንቅስቃሴ ተጀምሯል። እነዚህ የለውጥ ፍሬዎች ጥራት ላለው የቤተ ክርስቲያን ሕይወትና በጥምቀታችንና በሜሮናችን ጸጋ ሁላችንም የምንሳተፍበትን የስብከተ ወንጌል ተልእኮ ለመፈጸም ትልቅ ጠቀሜታ ያላቸው ግቦች ናቸው። እዚህ ላይ፣ ሲኖዶሳዊነት የቤተክርስቲያን ቅርጽ፣ ዐይነትና መዋቅር መገለጫ መሆኑን የሚያሳዩ ዐበይት ግቦችን እንዘረዝራለን፡-

- መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያንን በታሪክ ሂደት እንዴት እንደመራትና ዛሬም፣ በአንድነት የእግዚአብሔር ፍቅር ምስክሮች እንሆን ዘንድ እንዴት እንደሚጠራን ማስታወስ፤
- ለሰው ሁሉ የሚሆን፣ በተለይም በተለያዩ ምክንያቶች ለተገለሉ፣ ራሳቸውን የሚገልጹበትንና ስለ ሕዝበ እግዚአብሔር ግንባታ አስተዋጽኦ የማድረግ ድምፃቸው የሚሰማበትን አሳታፊና አካታች የቤተክርስቲያን ሕይወት መኖር፤
- መንፈስ ቅዱስ ለማህበረሰብና ለመላው የሰው ልጅ ቤተሰብ ጥቅም ሲል በነጻ የሚሰጣቸውን ልዩ ልዩ ጸጋዎችና ትሩፋቶች ማወቅና ማድነቅ፤
- ወንጌልን በመስበክና ይበልጥ ውብና ለኑሮ ምቹ የሆነ ዓለም ለመገንባት በሚደረገው ጥረት ኃላፊነት ለመውሰድ የሚያስችሉ አሳታፊ መንገዶችን መፈለግ፤
- በቤተክርስቲያን ውስጥ ኃላፊነትና ሥልጣን እንዴት ተግባራዊ እንደሚደረግና አስተዳደራዊ መዋቅሮችም እንዴት እንደሆኑ መመርመር፣ በወንጌል ላይ ያልተመሠረቱ ጭፍን ጥላቻዎችንና የተዛቡ አሠራሮችን ማጋለጥና መቀየር፤

- በማህበራዊ ውይይት፣ በፈውስ፣ በዕርቅ፣ በአካታችነትና አሳታፊነት፣ በዲሞክራሲ መልሶ ግንባታ፣ በወንድማማችነትና በማህበራዊ ወዳጅነት የዕድገት ጉዞ ውስጥ ክርስቲያን ማህበረሰብን እንደ ታማኝ አካልና አስተማማኝ አጋር መቁጠር፤
- በክርስቲያን ማህበረሰብ አባላት እንዲሁም በማህበረሰቦችና በሌሎች ማህበራዊ ቡድኖች መካከል፣ ለምሳሌ፣ በሌሎች የቤተ እምነትና የሃይማኖት ተከታዮች፣ በሲቭል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ በሕዝባዊ ንቅናቄዎች ወዘተ. መካከል፣ ግንኙነትን ማደስ፤
- በዓለም አቀፍ፣ በአህጉር፣ በብሔራዊና በአካባቢ ደረጃ በቅርቡ ለተገኙ ሲኖዶሳዊ ልምዶች እውቅናና አድናቆት  መስጠት።





3. ይህ የዝግጅት ሰነድ የሲኖዶሱን ጉዞ የሚያግዝ፣ በተለይም በልዩ አብያተ ክርስቲያናት የሚገኘውን ሕዝበ እግዚአብሔርን የማዳመጥና የማማከር የመጀመሪያ ሂደት (እ.አ.አ. ጥቅምት 2021- ሚያዝያ 2022) ለማቀላጠፍ፣ በዚህ ጉዞ የሚሳተፉትን ሁሉ ሐሳብ፣ ጉልበትና የፈጠራ ችሎታ ለማቀናጀትና የጥረታቸውንም ውጤት በቀላሉ ወደ ሌሎች ለማዳረስ የሚያገለግል መሣሪያ ነው። ከዚህ ዓላማ በመነሣት፣ ሰነዱ 1) የዘመኑን አንዳንድ ጉልህ መለያ ባህርያት በመዘርዘር ይጀምራል፤ 2) ሲኖዶሳዊነትን በትክክል ለመረዳትና ለመለመማድ የሚረዱ መሠረታዊ የነገረ መለኮት ማጣቀሻዎችን በአጭሩ ያብራራል፤ 3) በጉዞ ሂደት አስተንትኖንና ተመስጦን የሚያበረታቱ አንዳንድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሐሳቦችን ይለግሳል፤ 5) በጸሎትና በማጋራት መንፈስ ይህን የአስተንትኖ ሥራ መግለጽ የሚቻልባቸውን መንገዶችን ያሳያል። ሥራውን በተጨባጭ ለማስኬድ፣ ከዚህ የዝግጅት ሰነድ ጋር በተቀጽላነት የቀረበ የአዘገጃጀት ዘዴ መምሪያ ራሱን በቻለ ድረ ገጽ እንዲጫን ሐሳብ ቀርቧል።(3) ይህ ድረ ገጽ ለዚህ የዝግጅት ሰነድ የሚረዱና የሲኖዶሳዊነትን ርእሰ ጉዳይ የሚያጠናክሩ አንዳንድ ሐሳቦችን ያቀርባል። ከእነዚህም መካከል፣ ከዚህ በታች በተለያዩ ጊዜያት የተጠቀሱትን ሁለት ሐሳቦች አጉልተን ለማሳየት እንወዳለን። እነርሱም የጳጳሳት ሲኖዶስ የተመሠረተበትን 50ኛ ዓመት መታሰቢያ ክብረ በዓል ምክንያት በማድረግ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንሲስኮስ እ.አ.አ. ጥቅምት 17 ቀን 2015 ያደረጉት ንግግርና እ.አ.አ. በ2018 የታተመውና በዓለም አቀፍ የነገረ መለኮት ኮሚሽን የተዘጋጀው ሲኖዶሳዊነት በቤተክርስቲያን ሕይወትና ተልእኮ ውስጥ የሚለው ሰነድ ናቸው።

[3] (ንጽ. www.synod.va)



# 1. የክብሮነት ጉዞ ጥሪ

4. ሲኖዶሳዊ ጉዞ የሚከሰተው በህብረተሰብ ውስጥ በሚከሰቱ ታሪካዊ የለውጥ ወቅቶችና በቤተክርስቲያን ሕይወትና በቸልታ ሊታለፉ በማይችሉ ወሳኝ የሽግግር ምዕራፍ ውስጥ ነው። «የጊዜውን ምልክቶች የምንገመግማቸውና በወንጌል ብርሃን የምንተረጉማቸው» (GS, ቁ. 4)፣ ውጥረቶችና ተቃርኖዎች በበዙበት በዚህ ውስብስብ ሁኔታ ውስጥ ሆነን ነው። ከሲኖዶሱ ርእሰ ጉዳይ ጋር የቅርብ ግንኙነት ያላቸው አንዳንድ ሉላዊ እይታዎች እዚህ ላይ ተጠቅሰዋል። ሆኖም፣ ሙሉ ሥዕሉ/ዝግጅቱ በአጥቢያ ደረጃ ሊዳብርና ሊሟላ ይገባል።

5. በዓለም አቀፍ ደረጃ የተከሰተው አሳዛኙ የኮቪድ 19 ወረርሽኝ «ሁላችንም በአንድ ጀልባ ውስጥ የተሳፈርን፣ የአንዱ ሰው ችግር የሁሉም ችግር የሆነበት አንድ የዓለም ማኅበረሰብ አካል የመሆናችንን ስሜት በጊዜያዊነትም ቢሆን መልሶ አሳይቶናል። የምንድነው በጋራ ብቻ እንጂ አንድ ሰው ብቻውን ሊድን እንደማይችል ይበልጥ ተገንዝበናል። (FT, ቁ.32)። እንደዚሁም፣ ወረርሽኙ ቀደም ሲል ያለውን መበላለጥና አለመስተካከል ፈንድቶ እንዲወጣ አድርጎታል። የሰው ዘር በመሰባሰብና በመበታተን ሂደት ይበልጥ የተናጋ ይመስላል፤ በሁሉም የዓለም አካባቢዎች ያሉ ስደተኞች የሚያጋጥማቸው አሳዛኝ ሁኔታ አንድን የሰው ልጅ ቤተሰብ የሚከፋፍሉ ግድግዳዎች አሁንም ምን ያህል ትልቅና ጠንካራ እንደሆኑ ያሳያል። ላውዳቶ ሲ እና ፍራቴሊ ቱቲ የተባሉ ሐዋርያዊ

ሰነዶች የሰውን ዘር የሚከፋፍሉ ገደሎች ምን ያህል ጥልቅ እንደሆኑ ያስረዳሉ። እነዚህንም ትንተናዎች የድሆችንና የምድሪቱን ጩኸት ለመስማትና መንፈስ ቅዱስ በዘመናችን ጭምር የሚዘራውን የተስፋ ጭላንጭልና ብሩህ መጪ ጊዜ ለማየት ልንጠቀምባቸው እንችላለን። ‹‹ፈጣሪ ብቻችንን አይተወንም፤ የፍቅር ዕቅዱን ከቶ አይተውም፣ እንዲሁም እኛን በመፍጠሩም አይጸጸትም። የሰው ዘር መጪውን የጋራ ቤታችንን በጋራ የመገንባት ብቃት አለው›› (LS, ቁ. 13)።

6. ልዩነቶቹ ሰፋፊ ቢሆኑም፣ ይህ ሁኔታ መላውን የሰው ዘር በአንድነት ያስተሳስራል፤ ቤተ ክርስቲያን ከግለ ሰቦችና ማህበረ ሰቦች ጎን ሆና በርካታ ቀቢጸ ተስፋዎችን ያጋለጡ የለቅሶና የመከራ ልምዶችን ዳግመኛ እንዲያሰላስሉ፣ እና በፈጣሪ ቸርነትና በፍጥረታቱ ያለው ተስፋና እምነት እንዲለመልም የማድረግ ብቃትዋን ይፈታተናል። ይሁን እንጂ፣ ቤተ ክርስቲያን ራስዋ በውስጧ እምነት የማጣትና የመበስበስ አደጋ ሊገጥማት እንደሚችል መካድ አንችልም። በተለይ፣ በለጋዎችና በድኩማን ላይ ‹‹በበርካታ ካህናትና መነኮሳት ምክንያት የደረሰውን የጾታ ጥቃት፣ የጉልበት ጥቃትና የኅሊና ጥቃት›› ልንረሳ አንችልም። (4) ‹‹እንደ ሕዝበ እግዚአብሔር በሥጋም በነፍስም የተሰቃዩ የወንድሞቻችንንና እህቶቻችንን ሕመም የመሸከም ፈተና ሁሌም ያጋጥመናል።›› (5) የሰለባዎች ለቅሶ ሊራዘም የቻለው ቤተክርስቲያን በበቂ ሁኔታ መስማት ባለመቻልዋ ነው። እነዚህ ለመዳን የሚያስቸግሩ፤ በበቂ ሁኔታ ይቅር የማይባሉና ‹‹በአብሮነት ጉዞ›› ውስጥ እንቅፋት የሆኑ፣ አንዳንዴም እንቅፋት የሚፈጥሩ፣ ጥልቅ ቁስሎች ናቸው። መላዋ ቤተ ክርስቲያን ከታሪኳ የወረሰችውን የቤተ ክህነት ባህላዊ ሸክም እንዲሁም

4 ፍራንሲስኮስ፣ ለሕዝበ እግዚአብሔር የተላከ መልእክት (እ.አ.አ. ነሐሴ 20 ቀን 2018)፣ መግቢያ

5 ከላይ የተጠቀሰው፣ ቁ. 2

ከሥልጣን አጠቃቀም ጋር የተያያዙ የተለያዩ የጥቃት ዐይነቶችን ( የሥልጣን፣ የኢኮኖሚ፣ የኅሊና፣ የጾታ) መቋቋም ይጠበቅባታል። እንደ ቤተ ክርስቲያን የሁሉንም የሕዝበ እግዚአብሔር አባላት ንቁ ተሳትፎ ያላካተተ የተግባር ለውጥ ይኖረናል» (6) ብሎ ማሰብ አይቻልም። ስለሆነም፣ «በእነዚህ ወንጀሎች ፊት ሆነን የተሰማንን ፀፀትና ወንጀሎቹን በድፍረት ለመዋጋት ያለንን ቁርጠኝነት ለመግለጽ የሚያስፈልገውን የመለወጥ ጸጋና ውስጣዊ መቀደስ እንዲሰጠን» (7) ጌታችንን በጋራ እንለምነው።

. . . The whole Church is called to deal with the weight of a culture imbued with clericalism that she inherits from her history, and with those forms of exercising authority on which the different types of abuse are grafted . . .

[6] ከላይ የተጠቀሰው
[7] ከላይ የተጠቀሰው

7. እኛ ታማኞች ባንሆንም፣ መንፈስ ቅዱስ ግን በታሪክ ውስጥ መሥራቱንና ሕይወት ሰጪ ኃይሉን ማሳየቱን ይቀጥላል። ኩነቶችን ከነገረ መለኮት አንጻር መተርጎም ብቻ ሳይሆን፣ በፈተናዎች ውስጥ ክርስቲያናዊና ቤተ ክርስቲያናዊ የሕይወት መንገዶችን እንደገና ለማደስ የሚያስችሉ አዳዲስ የእምነት ቋንቋዎችና አዳዲስ ዘዴዎች እየዳበሩ ያሉት እያንዳንዱ የሰው ልጅ ቤተ ሰብ በተሸከማቸው ልዩ ልዩ መከራዎች በተቆፈሩ ጠባብ መንገዶች ምክንያት ነው። ይህም ጥቂት አብያተ ክርስቲያናት የስብሰባዎቻቸውንና የውይይቶቻቸውን ሂደት ከሕዝበ እግዚአብሔር ጋር ለማቀናጀት የሚያስችል ትልቅ ተስፋ እንዲሰንቁ አድርጓቸዋል።

ስብሰባዎቹና ውይይቶቹ ሲኖዶሳዊ መልክ በያዙባቸው ስፍራዎች ቤተክርስቲያናዊ ስሜት ጨምሯል፤ የሁሉም ተሳትፎ ለቤተክርስቲያናዊ ሕይወት አዲስ ኃይል ፈጥሯል። እ.አ.አ. በ2018 እና 2019 በተካሄዱ የሲኖዶስ ጉባኤዎች እንደተንጸባረቀው፣ የወጣቶች በቤተክርስቲያን ውስጥ ዋና ተዋናይ የመሆን ምኞትና በቤተክርሰቲያን ተልእኮ ውስጥ የሴቶች ሚናና ተሳትፎ እንዲጨምር የሚነሡ ጥያቄዎችም ተቀባይነት አግኝተዋል። በቅርቡ የትምህርተ ክርስቶስ መምህራን/ካቴኪስቶች አገልግሎት መጀመርና ሴቶች በመጽሐፍ ቅዱስ አንባቢነትና አገልጋይነት እንዲሳተፉ መፍቀድ የዚህ አቅጣጫ ማሳያ ናቸው።

8. ክርስቲያን ማህበረሰቦች በተለያዩ የዓለም አካባቢዎች የሚኖሩባቸውን የተለያዩ ሁኔታዎች መርሳት የለብንም። ቤተክርስቲያን አብዛኛውን ሕዝብ ከምታቅፍባቸውና ለመላው ህብረተሰብ የባህል ማንጸባረቂያ ማዕከል ከሆነችባቸው አገሮች ጎን ለጎን፣ ካቶሊካውያን አናሳ የሆኑባቸው ሌሎች አገሮችም አሉ። ከእነዚህ አገሮች በአንዳንዶቹ ውስጥ ካቶሊካውያን፣ ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር በመሆን፣ ስደት፣ አንዳንዴም ሁከትና አልፎ አልፎም ሰማእትነት ያጋጥማቸዋል። በአንድ በኩል ዓለማዊ አስተሳሰብ ሃይማኖትን ከሕዝብ ልብ በሚያርቅበት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ለሌሎች ነጻነት ከበሬታ የማይሰጥ ሃይማኖታዊ አክራሪነት በሚሰፍንበት ሁኔታ በክርስቲያን ማህበረሰብና እርሱም ከህብረተሰብ ጋር በሚኖረው ግንኙነቶች ውስጥ የአለመቻቻልና የሁከት ዐይነቶች ይፈጥራሉ። አንዳንድ ጊዜ ክርስቲያኖችም ተመሳሳይ አስተሳሰብ ከመያዛቸው የተነሣ በቤተክርስቲያን ውስጥ ጭምር መከፋፈልንና ተቃውሞን ይቀሰቅሳሉ። ከዚህ ሌላ፣ በቤተክርስቲያን

ውስጥ እንዲሁም በቤተክርስቲያንና በህብረተሰብ ግንኙነቶች መካከል በዘር፣ በጎሳ፣ በነገድ ወይም በሌላ ማህበራዊ ክፍፍሎች ወይም ባህላዊና መዋቅራዊ ሁከት ወዘተ. ምክንያት የሚፈጠሩ እንደ ገደል ማሚቶ የሚያስተጋቡ ስብራቶችን ድምጽ ማጤን ያስፈልጋል። እነዚህ ሁኔታዎች ‹‹በአብሮነት ጉዞ›› ትርጉም እና በጉዞው ተጨባጭ ተፈጻሚነት ላይ መሠረታዊ ተጽእኖ አላቸው።



9. ከዚህ አኳያ፣ ሲኖዶሳዊነት በመንፈስ ቅዱስ ሥራና የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት ራስዋን ታድስ ዘንድ ለተጠራችው ቤተክርስቲያን ዋና የጉዞ አቅጣጫዋ ነው። በተቀበለችው ተልእኮ መሠረት ስለ ቤተክርስቲያንና ስለ ተቋሞችዋ ልዩ ተስፋ መሰነቅ የሚቻለው፣ በዋናነት እያንዳንዱ ሰው የሚሳተፍበትንና አስተዋጽኦ የሚያደርግበትን የመስማት፣ የመወያየትና ማህበራዊ ግንዛቤ የማዳበር ሂደቶችን ለመጀመር በሚደረገው ውሳኔ ላይ በመመርኮዝ ነው። እንደዚሁም፣ «የአብሮነት ጉዞ» ውሳኔ የሁሉንም ጥቅም የመጠበቅ የጋራ ዓላማ ለሚያስፈልገው የሰው ልጅ ነቢያዊ ምልክት ነው። የአንድነትና የወንድማማችነት፣ የተሳትፎና የተደጋጋፊነት ብቃት ያላትና ለምትሰብከው ነገር ታማኝ የሆነች ቤተክርስቲያን፣ ከድሆችና ከሁሉ በሚያንሱት ጎን ለመቆምና ለእነርሱም ድምጽ መሆን ትችላለች። «በአብሮነት ለመጓዝ» ስለ እውነተኛ ሲኖዶሳዊ አስተሳሰብ ከመንፈስ ቅዱስ መማር ያስፈልገናል። ቤተክርስቲያን፣ ሰብአዊት ተቋም እስከሆነች ድረስ፣ ምን ጊዜም ቢሆን በድፍረትና በልበ ሙሉነት ለምትፈልገው «ቀጣይ ተሐድሶ» ወሳኝ የሆነውን የመለወጥ ሂደት መጀመር ይኖርብናል (UR, ቁ. 26)።

. . . to “journey together,” we need to let ourselves be educated by the Spirit to a truly synodal mentality, entering with courage and freedom of heart into a conversion process . . .

# 2. ሲኖዶሳዊ አቋም ያላት ቤተ ክርስቲያን

10. ‹‹እግዚአብሔር በሶስተኛው ሺህ ክፍለ ዘመን ከቤተክርስቲያን የሚጠብቀው የሲኖዶሳዊነት መንገድ ይህ ነው። ጌታ ከእኛ የሚፈልገው ነገር፣ በሆነ መልኩ፣ ‹‹ሲኖዶስ›› በሚለው ቃል ውስጥ ይገኛል›› (8)። ‹‹ይህ ጥንታዊና ክቡር ቃል በቤተ ክርስቲያን ትውፊት ውስጥ የሚገኝ ሲሆን፣ ትርጉሙም የሚመነጨው ከራእይ ጥልቅ ርእሰ ጉዳዮች ነው›› (9)። ‹‹ራሱን ‹እኔ መንገድ፣ እውነትና ሕይወት ነኝ› (ዮሐ. 14፡6) በማለት የሚያቀርበው ጌታ ኢየሱስ ነው። ‹‹የእርሱ ተከታዮች የሆኑት ክርስቲያኖች ደግሞ መጀመሪያ ‹የመንገዱ ተከታዮች› እየተባሉ ይጠሩ ነበር (ንጽ. የሐዋ. 9፡2፤ 19፥9፥23፤22፥4፤24፥14፥22)›› (10)። ከዚህ አኳያ ሲታይ፣ ሲኖዶሳዊነት ከቤተክርስቲያን ስብሰባዎችና ከጳጳሳት ጉባኤዎች በላይ እንጂ የቤተክርስቲያን የውስጣዊ አስተዳደር ጉዳይ ብቻ አይደለም። አባሎችዋ በሙሉ በአንድነት ሲጓዙ፣ በአንድነት ሲሰበሰቡና በስብከተ ወንጌል ተልእኮዋ በንቃት ሲሳተፉ ሴታፌነትዋ የሚገለጽበትና የሚታወቅበት የቤተክርስቲያን፣ የሕዝበ እግዚአብሔር ዐይነተኛ የአሠራርና የአኗኗር ስልት ይሆናል።›› (11) የሲኖዶሳዊት ቤተ ክርስቲያን ዋና ዋና ዘንጎች በዚህ መልኩ እንደ ድርና ማግ እርስ በርስ የተጠላለፉ በመሆናቸው፣ የሲኖዶሱ ርእሰ ጉዳይ አብሮነት፣ ተሳትፎና ተልእኮ እንዲሆን ሐሳብ ቀርቧል። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ፣ ይህ አተያይ የተመሠረተባቸውን አንዳንድ መሠረታዊ የነገረ መለኮት ማጣቀሻዎችን በአጭሩ እናቀርባለን።

8 ፍራንሲስኮስ፣ የጳጳሳት ሲኖዶስ 50ኛ ዓመት የምሥረታ በዓል ሲከበር ያደረጉት ንግግር

9 ITC, ቁ.3

10 ከላይ የተጠቀሰው

11 ከላይ የተጠቀሰው፣ ቁ. 6

11. በአንደኛው ሺህ ክፍለ ዘመን፣ የአብሮነት ጉዞ፣ ማለትም የሲኖዶሳዊነት ትግበራ፣ «በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ አንድነት አንድ የሆኑ ሰዎች» (12) ማህበር በመባል የምትታወቀው ቤተክርስቲያን የምትከተለው መደበኛ አካሄድ ነበር። በቤተክርስቲያን አካል ውስጥ ክፍፍል የሚፈጥሩትን ወገኖች በተመለከተ የቤተክርስቲያን አበው በመላው ዓለም ተበታትነው የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናትን ሱታፌ፣ በቅዱስ አጉስጢኖስ አገላለጽ፣ የተጠመቁ አማኞችን ሁሉ ህብረት፣(13) ተቃወሙ። በቤተክርስቲያን ሕይወት ውስጥ በሁሉም ደረጃ፣ ማለትም በአጥቢያ፣ በአውራጃና በአገር አቀፍ ደረጃ ለሚተገበረው ሲኖዶስና በመጨረሻም ለክርስቲያኖች የአንድነት ጉባኤ መነሻ የሆኑ ምክንያቶች እነዚህ ናቸው። በዚህ የቤተክርስቲያን ማዕቀፍና ሁሉንም ሰው በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ በማሳተፍ መርሆ መሠረት ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ «ቤተክርስቲያንና ሲኖዶስ አንድ ናቸው» (14) እስከ ማለት ደርሷል። ቤተክርስቲያን ለሥልጣን ተዋረድ ትልቅ ትኩረት በሰጠችበት በሁለተኛው ሺህ ክፍለ ዘመን ጭምር፣ ይህ አካሄድ አልተቋረጠም ነበር። ከክርስቲያኖች የአንድነት ጉባኤዎች ጎን ለጎን የሰበካና የአውራጃ ሲኖዶሶች ጉባኤዎችም መኖራቸው ተረጋግጧል። ቀኖናዊ እውነታዎችን በመወሰን ረገድ፣ ርእሳነ ሊቃነ ጳጳሳት የመላ ቤተክርስቲያንን እምነት ለማወቅ ሲሉ፣ ጳጳሳትን ለማማከር ፈለጉ። ይህንንም ያደረጉት «በእምነት ረገድ ‹የማይሳሳተውን›» (EG, ቁ. 119) የመላው ሕዝበ እግዚአብሔርን ሥልጣን በመጠቀም ነው።

... "Church and Synod are synonymous" ...

12 ቆጵሪያኖስ፣ « የጌታ ጸሎት፣ 23

13 አጉስጢኖስ፣ ደብዳቤ 194፣ 31

14 ዮሐንስ አፈወርቅ፣ በመዝሙረ ዳዊት ላይ የሰጠው አስተያየት 149

12. ሁለተኛው የቫቲካን ጉባኤ በዚህ የትውፊት እንቅስቃሴ ላይ የተመሠረተ ነው። «እግዚአብሔር ግን ሰዎችን በተናጠል፣ ያለ አንዳች የእርስ በርስ ትስስር ወይም ቁርኝት፣ እያንዳንዳቸውን ቅዱሳን አያደርጋቸውም፣ አያድናቸውምም። ይልቁንም ሰዎችን አንድ ሕዝብ፣ እርሱን በእውነት የሚቀበልና በቅድስና የሚያገለግል አንድ ሕዝብ እንዲሆኑ ፈለገ» (LG, ቁ. 9)። የሕዝበ እግዚአብሔር አባላት በጥምቀት አንድ የሆኑና «በክርስቶስ ፈቃድ አንዳንዶቹ መምህራን፣ ካህናትና በሌሎች ስም ምስጢራትን የሚያድሉ፣ ነገር ግን ሁላቸውም በክብርና የክርስቶስን አካል በመገንባት በምእምናን ሁሉ የጋራ ሥራ ውስጥ እውነተኛ እኩልነት ያላቸው ናቸው» (LG, ቁ. 32)። ስለዚህ፣የተጠመቁ፣ «የተሰጣቸውን ልዩ ልዩ የጸጋ ሙላት፣ መንፈሳዊ ጥሪና አገልግሎት ተጠቅመው» (15) በክርስቶስ ክህነታዊ፣ ነቢያዊና ንጉሣዊ ተግባራት የሚሳተፉ ሁሉ፣ በግልም እንደ መላው ሕዝበ እግዚአብሔርም፣ የስብከተ ወንጌል ንቁ ባለቤቶች ናቸው።

13. በምሥጢረ ጥምቀት አማካይነት በተቀቡት የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ የተነሣ « መላ ምእመናን እምነትን በተመለከተ እንደማይሳሳቱ» ሁለተኛው የቫቲካን ጉባኤ በአጽንኦት ገልጿል። «ይህን ልዩ ባህርይ የሚያሳዩት የእምነትን ጉዳዮች በተመለከተ ባላቸው ላዕላይ ሕዝባዊ የመረዳት ችሎታ፣ ‹በተዋረድ ከጳጳሳት አንሥቶ እስከ ምእመናን ድረስ› እምነትንና ግብረ ገብን በሚመለከቱ ጉዳዮች ባላቸው ሁሉን አቀፍ ስምምነት ነው» (LG, ቁ. 12)። ምእመናንን «ወደ እውነት ሁሉ» የሚመራው መንፈስ ቅዱስ ነው (ዮሐ. 16፡13)። በመንፈስ ቅዱስ ሥራ አማካይነት፣ «ከሐዋርያት የተወረሰው ይህ ትውፊት በቤተክርስቲያን ውስጥ ያድጋል»። ይህም የሆነው፣ ሕዝበ እግዚአብሔር ከትውልድ ወደ ትውልድ የተላለፉ እውነታዎችንና ቃላቱን በማወቅ» እንዲያድጉ ነው። ይህም የሚሆነው፣ እነዚህን ነገሮች በልባቸው በክብር የሚይዙ፣(ንጽ ሉቃ. 2፡19፣51)፣ የሚለማመዷቸውን መንፈሳዊ እውነታዎች በጥልቀት የሚያውቁና በጵጵስና የሥልጣን ውርስ የእውነትን እውነተኛ ጸጋ የተቀበሉ (DV, ቁ. 8)

[15] ITC, ቁ.6

ምእመናን በሚያደርጉት አስተንትኖና ጥናት ነው። በእርግጥ፣ በመንፈሳዊ እረኞቹ ሥር የተሰባሰበው ይህ ሕዝብ ለቤተክርስቲያን የተሰጠው የቃለ እግዚአብሔር ቅዱስ ባለአደራ፣ በሐዋርያት ትምህርት፣ በወንድማማችነት ሱታፌ፣ እንጀራን በመቁረስና በጸሎት የሚጸና ነው። ይህም የሆነው፣ «የእምነትን ቅርስ አጥብቆ መያዝ፣ መለማመድና መስበክ፣ የጳጳሳትና የምእመናን የጋራ ጥረት እንዲሆን ነው» (DV, ቁ. 10)።

. . . The consultation of the People of God does not imply the assumption within the Church of the dynamics of democracy based on theprinciple of majority . . .

14. የመላ ቤተ ክርስቲያን እምነት «እውነተኛ መጋቢዎች፣ ተርጓሚዎችና ምስክሮች»(16) እንዲሆኑ እግዚአብሔር የመረጣቸው መንፈሳዊ እረኞች በአደራ የተሰጣቸውን መንጋ ለማዳመጥ መፍራት የለባቸውም። ሕዝበ እግዚአብሔርን ማማከር በቤተክርስቲያን ውስጥ በአብላጫ ድምጽ መርሆ ላይ የተመሠረተውን የዲሞክራሲአዊ እንቅስቃሴ መኖር የሚያመለክት አይደለም፤ ምክንያቱም፣ በእያንዳንዱ የሲኖዶስ ሂደት በሚደረገው ተሳትፎ ውስጥ ያለው፣ የተቃራኒ

[16] ፍራንሲስኮስ፣ የጳጳሳት ሲኖዶስ የተመሠረተበት 50ኛ ዓመት ሲከበር ያደረጉት ንግግር

ፍላጎቶች ውክልና ሳይሆን ለጋራ የስብከተ ወንጌል ተልእኮ የሚሆን የጋራ ስሜት ነው። በሌላ አነጋገር፣ ‹‹የሥልጣን ተዋረድ ባለው ማህበረሰብ ውስጥ›› ብቻ የሚከናወን የቤተክርስቲያን ሂደት ነው (17)። አንዲት እምነት ባላት ሙሉ ቤተክርስቲያን ውስጥ የጋራ ስምምነት ሊረጋገጥ የሚችለው በሕዝበ እግዚአብሔር ተፈጥሮአዊ የእምነት ባህርይና በመንፈሳዊ እረኞች የሥልጣን ተግባር ነው። በራሳቸው ሳይሆን፣ ‹‹በክርስቶስ ነቢያዊ ተልእኮ የሚሳተፍ›› (LG, ቁ. 12) ሕዝበ እግዚአብሔርን በማማከር መንፈስ ቅዱስ ለቤተክርስቲያን የሚናገረውን ነገር ለይተው እንዲያውቁ የተጠሩ ጳጳሳት የሚሳተፉበት እያንዳንዱ የሲኖዶስ ሂደት ቤተክርስቲያንን የሚያሳድግ ‹‹የአብሮነት ጉዞ›› ጉልህ ማሳያ ነው። ቅዱስ ቤነድክቶስ በአጽንኦት እንደተናገረው፣ ‹‹ጌታ አብዛኛውን ጊዜ ሰዎች ሊከተሉት የሚገባውን ትክክለኛ መንገድ የሚያሳየው›› (18) በማህበረሰብ ውስጥ ትልቅ የሥልጣን ቦታ ለሌላቸው (ማለትም ለታናናሾች) ነው። ስለዚህ፣ ሥርዓት ባለው ሁኔታ በሚካሄደው ሲኖዶሳዊ ጉዞ ውስጥ፣ ሐዋርያው ጳውሎስ ለምእመናን ‹‹መንፈስን አታጥፉ፤ ትንቢትን አትናቁ፣ ሁሉን ፈትኑ፣ መልካሙንም ያዙ›› (1ኛ ተሰሎ. 5፡19-21) በማለት እንዳሳሰበው፣ ጳጳሳት ወደ ሁሉም ሰው ዘንድ ለመድረስ ትኩረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

. . . a synodal Church is a Church "going forth," a missionary Church "whose doors are open" . . .

17 ITC , ቁ. 69

18 ቤነድክቶስ ፣ ደንብ፣ 3.3

15. ሁላችንም የተጠራንበት መንፈሳዊ ጉዞ የሲኖዶሳዊት ቤተክርስቲያንን ፊትና ቅርጽ ከመፈለግ በላይ ትርጉም ያለው ነው። በዚህ ጉዞ ላይ «ሁሉም ሰው የሚማረው ነገር አለው። ሕዝበ ምእመናን፣ የጳጳሳት ማህበር፣ የሮማ ጳጳስ፣ ሁላቸውም እርስ በርስ ይደማመጣሉ፤ ሁላቸውም «ለአብያተ ክርስቲያናት የሚናገረውን ነገር ለማወቅ «የእውነት መንፈስ» (ዮሐ. 14፡17) የሆነውን መንፈስ ቅዱስን ያዳምጣሉ። (19) የቤተክርስቲያኒቱ የአንድነት መርህና መሠረት የሆኑት የሮማ ጳጳስ አንዲትና ዐይነተኛ የሆነች የካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ሕልውና መሠረት የሆኑትን ጳጳሳትና ልዩ አብያተ ክርስቲያናትን በሙሉ በልበ ሙሉነትና በድፍረት ወደ ሲኖዶሳዊነት መንገድ እንዲገቡ ይጠሯቸዋል (ንጽ. LG, ቁ. 23)። በዚህ «የአብሮነት ጉዞ» የተለያዩ ጸጋዎችን፣ ትሩፋቶችንና አገልግሎቶችን አንድ የሚያደርጋቸው መንፈስ ቅዱስ ሱታፌ ለተልእኮ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ፣ ይኸውም ሲኖዶሳዊት ቤተ ክርስቲያን «ወደ ፊት የምትራመድ»፣ «በሯን ክፍት ያደረገች» ልኡክ ቤተክርስቲያን መሆንዋን እንድናውቅ ይረዳን ዘንድ እንለምነዋለን። (EG, ቁ. 46)። ይህም በጥምቀት አንድ ከሆንነባቸው ሌሎች አብያተ ክርስቲያናትና ክርስቲያን ማህበረሰቦች ጋር ግንኙነቶችን የማጥበቅ ጥሪንም ያካትታል። ስለዚህ፣ «የአብሮነት ጉዞ» ገጽታ ሰፋ ያለና «ደስታውንና ተስፋውን፣ ኀዘኑንና ጭንቀቱን» የምንጋራውን መላውን የሰው ዘር የሚያቅፍ ነው።


(GS, ቁ.1)። ሲኖዶሳዊት ቤተክርስቲያን፣ በተለይ የሁሉንም ጥቅም የማስከበር የጋራ ዓላማ ለሌላቸው አገሮች፣ ነቢያዊ ምልክት ናት። ሲኖዶሳዊነትን ተግባር ላይ ማዋል ዛሬ ለቤተክርስቲያን «ሁሉን አቀፍ የድኅነት ምሥጢር» (LG, ቁ.48)፣ «ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት የመፍጠርና የመላው የሰው ዘር አንድነት ምልክትና መሣሪያ» (LG, ቁ. 1) የመሆን ጉልህ መንገድ ነው።



[19] ፍራንሲስኮስ፣ ፍራንሲስኮስ፣ የጳጳሳት ሲኖዶስ የተመሠረተበት 50ኛ ዓመት ሲከበር ያደረጉት ንግግር

# 3. ቅዱሳት መጻሕፍትን ማዳመጥ

16. ለአብያተ ክርስቲያናት «የአብሮነት ጉዞ» ብርሃንና ሕይወት የሚሰጠው የእግዚአብሔር መንፈስ፣ ለደቀ መዛሙርትና የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው ተግባራዊ ለሚያደርጉ የደቀ መዛሙርት ትውልዶች ቃል የተገባላቸው፣ በክርስቶስ ተልእኮ ውስጥ የሚሠራው ያው መንፈስ ነው። በጌታ የተስፋ ቃል መሠረት፣ መንፈስ ቅዱስ ራሱን የኢየሱስን ወንጌል በማስቀጠል ብቻ አይወስንም፤ ይልቁንም የክርስቶስን ትንሣኤ ጥልቅ ትርጉም ያሳያል፣ የቤተክርስቲያንን ጉዞ ለማስቀጠል የሚያስፈልጉ ውሳኔዎችን ያበረታታል (ንጽ. ዮሐ. 14፡25-26፤ 15፡26-27፤ 16፡12-15)። ስለዚህ፣ ሲኖዶሳዊት ቤተ ክርስቲያንን የመገንባት ጉዞአችን ከመጽሐፍ ቅዱስ በተወሰዱ ሁለት «ምስሎች» መመራት ይኖርበታል። አንደኛው ከስብከተ ወንጌል ጉዞ ጋር አብሮ የሚሄድ «ማህበረሰባዊ ምስል» ሲሆን፣ ሌላኛው ጴጥሮስና የጥንት ክርስቲያኖች እምነትን በመጋራት ረገድ የነበራቸውን ያልተገባ ገደብ የማስቀመጥ ስጋት የሚያውቁበት የመንፈስ ቅዱስ ልምድ ነው። ጌታን በመከተልና መንፈስ ቅዱስን በመታዘዝ የሚገኘው የአብሮነት ጉዞ ሲኖዶሳዊ ልምድ፣ በእነዚህ ሁለት የመገለጥ ባህርያት ላይ በተመረኮዘ አስተንትኖ በወሳኝ መልኩ ሊነቃቃ ይችላል።



17. የመጀመሪያው ምስል በመሠረታዊ አቋሙ፣ ኢየሱስ በወንጌል ውስጥ ራሱን የገለጠበትን፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት መምጣት ያወጀበትን መንገድ ያሳያል። በዋናነት ሶስት ተዋንያን (ሲደመር አንድ) በዚህ ሂደት ውስጥ ተካትተዋል። የመጀመሪያው ተነሣሽነቱን የወሰደው፣ «ያለ አድልዎ» ስለ እግዚአብሔር መንግሥት መምጣት ቃሉንና ምልክቶቹን በመዝራት ቀዳሚነቱን የወሰደው ዋናው ገጸ ባህርይ ኢየሱስ ነው። በብዙ መንገድ፣ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር «ለተለዩ» እና ማህበረሰቡ «ላገለላቸው» ወገኖች (በወንጌል ቋንቋ ለኃጢአተኞችና ለነዳያን) ልዩ ትኩረት ይሰጣል። በቃሉና በምግባሩ፣ በእግዚአብሔር አብ ስምና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ከክፋት ነጻ መሆንንና ወደ ተስፋ መመለስን ይሰጣል። የጌታ የሚያቀርባቸው ጥሪዎች የተለያዩ ቢሆኑም፣ ምላሻቸውና የጋራ ባህርያቸው እንደሚያሳየው ግን፣ እምነት ምን ጊዜም የሰዎች ማንነት መመዘኛ መሆኑን ነው፤ በዚህ ጥሪ አማካይነት አቤቱታቸው ይሰማል፤ ችግራቸው ይቃለላል፤ መገኘታቸው ይወደሳል፤ ክብራቸው በእግዚአብሔር ፊት ይገለጣል፣ በማህበረሰብ ዘንድም ዳግመኛ ይታደሳል።

18. በመሠረቱ፣ የስብከተ ወንጌልን ሥራና የድኅነት መልእክት መረዳት የሚቻለው ኢየሱስ ለሰፊው ሕዝብ፣ (ወንጌላት ሕዝብ ለሚሉት)፣ ማለትም እርሱን በየመንገዱ ለሚከተሉና አንዳንዴም አንዳች ምልክትና የድኅነት ቃል ፍለጋ እርሱን ለሚከታተሉ ሰዎች ሁሉ ያለመታከት ሲገለጥ ብቻ ነው። ይህም በራእይ ትዕይንት ውስጥ ሁለተኛው ተዋናይ ነው። ወንጌል የሚሰበከው ለምሁራን ወይም ለተመረጡ ጥቂቶች ብቻ አይደለም። የኢየሱስ የውይይት ተካፋይ ተራው «ሕዝብ» ነው፤ ከእግዚአብሔር ጸጋና ከድኅነት ጥሪ ጋር በቀጥታ የሚያገናኘው ሰብአዊ የሆነ «ማንኛውም ሰው» ነው። ምስክሮችን በሚያስደንቅና አንዳንዴም ቅሌት ውስጥ በሚያስገባ መንገድ፣ ኢየሱስ ከሕዝብ መካከል የሚወጡትን ሁሉ እንደ የውይይት ተካፋዮች ይቀበላቸዋል፤እርሱ ከሚያመጣው በረከት

መገለል ያልፈለገችውን የከነዓናዊቷን ሴት ልባዊ ምሬት ያዳምጣል (ንጽ.ማቴ.15፡21-28)፤ ማህበራዊና ሃይማኖታዊ ተቀባይነት ባይኖራትም፣ ከሳምራዊቷ ሴት ጋር ለመነጋገር ፈቀደ (ንጽ. ዮሐ. 4፡1-42)፤ በሃይማኖት ረገድ ከጸጋ ውጭ ነው ተብሎ የተተወውን የአንድ ዕውር ሰውን የእምነትና የምስጋና ሥራ ተቀበለ (ንጽ. ዮሐ. 9)።

. . . The proclamation of the Gospel is not addressed only to an enlightened or chosen few. Jesus' interlocutor is the "people" of ordinary life,
the "everyone" of
the human condition . . .

19. አንዳንዶች ኢየሱስን በደቀ መዝሙር ታማኝነት በግልጽ ይከተሉታል፣ ሌሎቹ ደግሞ ወደ መደበኛ ኑሯቸው እንዲመለሱ ይጠየቃሉ፤ ሆኖም ሁላቸውም ያዳናቸውን የእምነት ኃይል ይመሰክራሉ (ንጽ. ማቴ. 15፡28)። ኢየሱስን ከሚከተሉት መካከል፣ እርሱ ራሱ ከመጀመሪያው የጠራቸው፣ ሕዝቡን ከመገለጥና ከሚመጣው የእግዚአብሔር መንግሥት ጋር የማገናኘት ሥልጣን የተሰጣቸው ሐዋርያት ጎልተው ይታያሉ። የሶስተኛው ተዋናይ ትዕይንት የሚመጣው ለፈውስ ወይም ለለውጥ ሳይሆን፣ ከኢየሱስ ጥሪ ጋር ስለሚገጣጠም ብቻ ነው። የሐዋርያት መመረጥ የሥልጣንና

የመለየት ልዩ ክብር ሳይሆን፣ የበረከትና የወዳጅነት አሳታፊ አገልግሎት ጸጋ ነው። ከሙታን በተነሣው ጌታ ከተሰጠው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ የተነሣ ሐዋርያት ኢየሱስን መተካት ሳይሆን፣ የኢየሱስን ቦታ ያስከብራሉ፣ የእርሱን ሀልዎት ማድበስበስ ሳይሆን፣ ከእርሱ ጋር ያገናኛሉ።

. . . The election of the apostles is not the privilege of an exclusive position of power and separation but the grace of an inclusive ministry of blessing and fellowship . . .

20. ቤተክርስቲያን ይበልጥ ራስዋን ትሆን ዘንድ በጥልቀት ሊጤንና ሊዳሰስ የሚገባው ምስልና ምስጢር ቢኖር ኢየሱስ፣ መላው ሕዝብ እና ሐዋርያት ናቸው። ከእነዚህ ከሶስቱ ተዋንያን አንዱም ቢሆን ከትዕይንቱ ሊቀር አይችልም። ኢየሱስ ከሌለና ሌላ ሰው የእርሱን ቦታ ከወሰደ፣ ቤተክርስቲያን በሐዋርያትና በሕዝብ መካከል የተደረሰ ተራ ስምምነት ይሆናል፤ ውይይቱም የፖለቲካ ሴራ ጨዋታን ተከትሎ ፈራሽ ይሆናል። ኢየሱስ የሾማቸውና መንፈስ ቅዱስ ያዘዛቸው ሐዋርያት ከሌሉ፣ ከወንጌላዊ እውነት ጋር ያለው ግንኙነት ይበጠሳል፤ ሕዝቡ ኢየሱስን ቢቀበል ባይቀበል፣

ስለ እርሱ ለሚወራው አፈ ታሪክ ወይም ርእዮተ ዓለም ተጋላጭ መሆኑ አይቀርም። ሕዝብ ከሌለ፣ የሐዋርያትና የኢየሱስ ግንኙነት የሃይማኖት አንጃና ራስ ተኮር ብቻ ይሆናል፤ እግዚአብሔር ለሰው ሁሉ ከሚሰጠውና ድኅነቱን ከሚለግሰው ራስን በቀጥታ ከመግለጥ የሚመነጨው ስብከተ ወንጌል ብርሃንነቱን ያጣል።

. . . The insidiousness that divides . . .
manifests itself indifferently in the forms
of religious rigor, of moral injunction
. . . and of the seduction
of a worldly political . . .

21. ከዚህ ሌላ፣ «ትርፍ» ተዋናይ፣ ተቃዋሚ አለ፤ እርሱም የተቀሩትን ሶስቱን ነጣጥሎ የሚያሳይ ዲያብሎሳዊ ተዋናይ ነው። የመስቀል ተስፋ አስጨንቋቸው ትተው የሚሄዱ ደቀ መዛሙርትና ተለዋዋጭ ስሜት ያላቸው ሕዝቦች አሉ። የሚከፋፍልና የአብሮነት ጉዞን የሚያሰናክል የተንኮል ሥራ በግድ የለሽነት የሚገለጠው በሃይማኖታዊ የፍጹምነት ዐይነቶች፣ ከኢየሱስ የሚበልጥ ግብረ ገባዊ ትዕዛዝ አለኝ ብሎ በሚመጻደቅ መንፈስና መናፍስትን ከመለየት የበለጠ ውጤታማ ነኝ በሚለው በዓለማዊ የፖለቲካ ጥበብ ፈተና ነው። «ከአራተኛው ተዋናይ» ተንኮል ለማምለጥ በቀጣይነት መለወጥ ያስፈልጋል። ለዚህም የመቶ አለቃው የቆርኔሌዎስ ታሪክ (ንጽ. የሐዋ. 10)፣ ለሲኖዶሳዊት ቤተክርስቲያን ወሳኝ ማጣቀሻ የሆነው የጥንቱ የኢየሩሳሌም «ጉባኤ» (ንጽ. የሐዋ. 15) በአብነት ይጠቀሳሉ።



## የከውጥ ክጥፍ ኅፃቤ፡ -
## ጴጥሮስና ቆርኔሌዎስ (የሐዋ. 10)



22. ከሁሉ አስቀድሞ ድርጊቱ ስለተለወጠውና የምስራች ስለተቀበለው ቆርኔሌዎስ ይተርካል። ቆርኔሌዎስ አረማዊ፣ ምናልባትም ሮማዊ፣ በቅኝ ገዢ ወራሪ ሠራዊት ውስጥ የመቶ አለቃ (ዝቅተኛ ማዕረግተኛ) የነበረና በሁከትና በጥቃት የሚያምን ሰው ነው። ሆኖም፣ በጸሎትና ለሕዝብ ምጽዋት በማድረግ የሚተጋ፣ ማለትም እግዚአብሔርን የሚያመልክና ባልንጀራውን የሚንከባከብ ሰው ነው። እርሱም በቤቱ ውስጥ ሳለ በድንገት የእግዚአብሔር መልአክ ወደርሱ ቤት ገብቶ በስሙ ጠራው፣ የተልእኮ ቃል እንዲልክ አበረታታው፤ ጴጥሮስን እንዲጠሩለት ሎሌዎቹን ወደ ጃፋ ላከ። ይህም አንዳንዶቹ ርኩስ የሆኑ እንስሳትን አርዶ እንዲበላ በተመሳሳይ ቀን በራእይ ለታዘዘው ለጴጥሮስ መለወጥ የታሪክ አጋጣሚ ሆነለት። የጴጥሮስ ምላሽ ግን «ጌታ ሆይ፣ ይህ አይሆንም» የሚል ነበር (የሐዋ. 10፡14)። ለእርሱ የሚናገረው ጌታ መሆኑን ቢያውቅም፣ ፈርጠም ብሎ እምቢ ያለበት ምክንያት ትዕዛዙ የሙሴን ሕግጋት የሚጥስና ከእርሱ ሃይማኖታዊ ማንነት ጋር የማይጣጣም ስለነበረ ነው፤ ይኸውም እነዚህ የሙሴ ሕግጋት የአይሁድ መመረጥ ከሌሎች ሰዎች የመለየትና የመገለል ማሳያ መንገድ ተደርገው ስለሚታሰቡ ነው።

23. ሐዋርያው ጴጥሮስ በዚህ ትዕዛዝ ምክንያት እጅጉን ተጨነቀ፣ ስለሆነው ነገር ምንነት ሲገረምና ሲያሰላስል ሳለ ቆርኔሌዎስ የላካቸው ሰዎች መጡ፤መንፈስም ሰዎቹ የእርሱ መልእክተኞች እንደሆኑ አመለከተው። ጴጥሮስም ኢየሱስ በአትክልት ስፍራ ሳለ የተናገረውን ቃል በሚያስታውስ መልኩ «እነሆ፣ የምትፈልጉኝ እኔ ነኝ» ሲል መለሰላቸው (የሐዋ. 10፡21)። ይህ እውነተኛና ተገቢ መለወጥ ነው፤ የራስን ባህላዊና ሃይማኖታዊ ፈርጆች የመተው አስጨናቂና እጅግ ፍሬያማ መንገድ ነው። ጴጥሮስ ምንጊዜም ውግዝ ብሎ የሚያስበውን ምግብ ከአረማውያን ጋር ለመብላት ፈቀደ፤ ይህንንም ያደረገው ምግቡ ከእግዚአብሔርና ከሌሎች ጋር የሚደረግ የሕይወትና የሱታፌ መሣሪያ መሆኑን ስለተገነዘበ ነው። የራእዩንም ትርጉም የተረዳው ከሰዎች ጋር በመገናኘት፣ እነርሱንም በመቀበል፣ ከእነርሱ ጋር በመጓዝና ወደ ቤቶቻቸው በመግባት ነው። በእግዚአብሔር ፊት ዋጋ ቢስ ሰው የለም፣ በመመረጥ ምክንያት የመጣው ልዩነት አገልግሎትንና ሁሉን አቀፍነትን መመስከርን እንጂ ፍጹም ምርጫን አያመለክትም።


. . . no human being is unworthy in the eyes of God, and the difference established by election does not imply exclusive preference but service and witnessing of a universal breadth . . .

( . . 10 38)

‹‹ ›› ( . 11 3)

‹‹ ››





# 4. ሲኖዶሳዊነት በተግባር፡-
# ሕዝበ እግዚአብሔርን የማማከር መንገዶች

25. በእግዚአብሔር ቃል የሚመራውና በትውፊት ላይ የተገነባው ሲኖዶሳዊ መንገድ በሕዝበ እግዚአብሔር ተጨባጭ ሕይወት ላይ የተመሠረተ ነው። ዓላማው፣ ሲኖዶሳዊነቱና ዘዴው ልዩና ዐይነተኛ ነው። በሌላ አነጋገር፣ እያደገ የሚሄድ ሲኖዶሳዊ መለወጥ፣ ለክርስቲያን ማህበረሰብ የሚሰጠውን ፍሬ ወዲያውኑ ማግኘት የሚያስችለውን የግንባታ ቦታ ወይም የሙከራ ትግበራ ይመስላል። በአንጻሩ፣ በተለያዩ ደረጃዎችና በተለያየ የስሜት ግለት በተግባር የሚገለጹ ሲኖዶሳዊ ተሞክሮዎችን ብቻ ያመለክታል። የሚጓዙበትን አቅጣጫ ለመረዳት የሚረዱ መሠረታዊ ነገሮች እንደየጥንካሬአቸውና ስኬታቸው እንዲሁም እንደየውስንነታቸውና ችግሮቻቸው ይቀርባሉ። በእርግጥ እዚህ ላይ በአሁኑ ሲኖዶሳዊ ጉዞ የተገኙ ተሞክሮዎችን ብቻ ሳይሆን፣ ሲኖዶሳዊነት የሚለው ቃል ባይታወቅምና ጥቅም ላይ ባይውልም፣ በመደበኛ ሕይወት ውስጥ «በአብሮነት ጉዞ» የታዩትንም ልምዶች መጥቀስ ይቻላል።

## መሠረታዊ ጥያቄ

26. ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው፣ ይህን የሕዝበ እግዚአብሔር ውይይት የሚመራው መሠረታዊ ጥያቄ የሚከተለው ነው፡-


ሲኖዶሳዊት ቤተክርስቲያን፣ ወንጌልን ስትሰብክ «አብራ ትጓዛለች»። ይህ «የአብሮነት ጉዞ ዛሬ በእናንተ ልዩ ቤተክርስቲያን ውስጥ የሚከናወነው እንዴት ነው? «በአብሮነት ጉዟችን» ለማደግ መውሰድ የሚገባንን እርምጃዎች እንወስድ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ ምን ይመክረናል?

እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ማድረግ የሚጠበቅባችሁ ነገር፡-

ሀ) በልዩ ቤተክርስቲያናችሁ ውስጥ መሠረታዊው ጥያቄ የሚያነሣቸው ተሞክሮዎች ምንድን ናቸው? ብላችሁ ራሳችሁን መጠየቅ፤

ለ) እነዚህም ተሞክሮዎች በጥልቀት መልሶ መላልሶ ማንበብ፤ እነዚህ ልምዶች ምን ዐይነት ደስታን ያጭራሉ? ያጋጠሟቸው መሰናክሎችና ችግሮችስ ምንድን ናቸው? ያጋለጧቸው ቁስሎች ምንድን ናቸው? ምን ዐይነት ማስተዋልን አስገኙ?

ሐ) ፍሬ ነገሩን ሰብስቦ ማጋራት፡- በእነዚህ ተሞክሮዎች ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ድምፅ የሚያስተጋባው የት ነው? ከእኛስ የሚጠይቀው ነገር ምንድን ነው? የሚደገፉ ነጥቦች፣ የለውጥ ተስፋዎች፣ መወሰድ የሚገባቸው እርምጃዎች ምንድን ናቸው? ስምምነታችን ምንድነው? ለልዩ ቤተክርስቲያናችን የተከፈቱ መንገዶችስ የትኞቹ ናቸው?





27. በመሠረታዊ ጥያቄ በተቀሰቀሰው ጸሎት፣ አስተንትኖና መጋራት ውስጥ ሲኖዶሳዊነት ‹‹የቤተክርስቲያን መሠረታዊ ገጽታ›› (20) ሆኖ የሚገለጽባቸውን ሶስት ደረጃዎች ማስተዋል ያስፈልጋል።

- ቤተክርስቲያን በመደበኛነት የምትኖርበትና የምትሠራበት፣ በአንድነት የሚጓዝና ጌታ ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ወንጌልን እንዲሰብክ በጠራው ጉባኤ የሚሳተፍ የሕዝበ እግዚአብሔር ባህርይ ያላት መሆንዋን የሚገልጽ ደረጃ። ይህ ደረጃ የሚገለጸው ‹‹የእግዚአብሔርን ቃል በሚሰማውና መሥዋዕተ ቅዳሴ በሚያከብረው ክርስቲያን ማህበረሰብ፣ በወንድማማችነት ሱታፌ እንዲሁም በሁሉም ደረጃዎችና በተለያዩ አገልግሎቶችና ሚናዎች መካከል ያለውን ልዩነት አውቆ በማህበረሰቡ ሕይወትና ተልእኮ በሚጋራው በመላ ሕዝበ እግዚአብሔር የጋራ ኃላፊነትና ተሳትፎ ነው።›› (21)

- የቤተክርስቲያን ሲኖዶሳዊ ባህርይ ተቋማዊ በሆነ መልኩ በአጥቢያ፣ በአካባቢና በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚገለጽበትና በነገረ መለኮታዊና ቀኖናዊ አመለካከት አንጻር የተቃኘው የቤተክርስቲያን መዋቅሮችና ሂደቶች ደረጃ።

- ቤተክርስቲያን በቤተክርስቲያናዊ ሥነ ሥርዓት በተወሰኑ ልዩ ሂደቶች መሠረት ሥልጣን ባለው አካል የምትጠራባቸው ሲኖዶሳዊ ሂደቶችና ኩነቶች ደረጃ።

ከስነ አመክንዮ አኳያ ልዩነት ቢኖራቸውም፣ እነዚህ ሶስቱ ደረጃዎች እርስ በርስ የሚናበቡ በመሆናቸው፣ በጥምረትና በአንድነት መታየት ይኖርባቸዋል፤ ያለበለዚያ፣ ተጻራሪ ምስክርነት ስለሚተላለፍ፣ የቤተክርስቲያን ተአማኒነት ይሸረሸራል። በመዋቅሮችና በሂደቶች ውስጥ ካልተዋሐደ፣ የሲኖዶሳዊነት ዘይቤ ከሐሳብነትና ከምኞት ደረጃ ወደ ሽንገላ ደረጃ ዝቅ ይላል፤ ሂደቶችና ኩነቶች ደግሞ በበቂ ሁኔታ ካልተነቃቁ፣ ወደ ባዶ ሥነ ሥርዓትነት ይቀየራሉ።

---

[20] ITC , ቁ. 70

[21] ከላይ የተጠቀሰው፤

28. ከዚህ በተጨማሪ፣ ተሞክሮዎች እንደገና ሲተነተኑ፣ «የአብሮነት ጉዞን» መረዳት የሚቻለው እርስ በርስ በጥብቅ ከተሳሰሩ ሁለት የተለያዩ ገጽታዎች አንጻር መሆኑን ማስተዋል ያስፈልጋል። የመጀመሪያው ገጽታ የልዩ አብያተ ክርስቲያናትን ውስጣዊ ሕይወት፣ በእነርሱም መዋቅር ውስጥ ያሉ ክፍሎችን በዋናነትም በምእመናንና በመንፈሳዊ እረኞቻቸው፣ የሰበካ ሲኖዶስን ጨምሮ በሕገ ቀኖና ዲሲፕሊን በተመለከቱ ተሳታፊ አካላት እንዲሁም በእነርሱ ውስጥ በሚገኙ ማህበረሰቦች በተለይም በቁምስናዎች መካከል ያሉ ግንኙነቶችን ይመለከታል። ቀጥሎም በጳጳሳትና በሮማ ጳጳስ መካከል ያሉ ግንኙነቶችን እንዲሁም በሲኖዶሳዊነት መካከለኛ አካላት (በፓትሪያርካዊና በዐቢይ የሀገረ ስብከት በሚመሩ አብያተ ክርስቲያናት የጳጳሳት ሲኖዶሶች፣ በአብያተ ክርስቲያናት የበላይ ባለሥልጣናትና በባለሥልጣናት ጉባኤዎች እንዲሁም በብሔራዊ፣ በዓለም አቀፍና በአህጉር ደረጃ በተቋቋሙ የጳጳሳት ጉባኤዎች) መካከል ያሉ ግንኙነቶችንም ይመለከታል። ከዚያም እያንዳንዱ ልዩ ቤተክርስቲያን በውስጡ ያቀፋቸው የተለያዩ ገዳማዊ፣ የምንኩስናና የድንግልና ሕይወት፣ የምእመናን ማህበራትና ንቅናቄዎች፣ ልዩ ልዩ የቤተክርስቲያንና የቤተክርስቲያን ተቋማት (ትምህርት ቤቶች፣ ሆስፒታሎች፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ድርጅቶች፣ የበጎ አድራጎትና የእርዳታ ድርጅቶች፣ ወዘተ.) የሚያበረክቱትን አስተዋጽኦ ያካትታል። በመጨረሻም፣ ይህ ገጽታ የአንዲት ጥምቀት ጸጋ ተጋሪ ከሆንንባቸው ሌሎች ክርስቲያን ቤተ እምነቶች ወንድሞችና እህቶች ጋር ያሉንን ግንኙነቶችና የጋራ ዕቅዶች ያካትታል።

29. ሁለተኛው ገጽታ ሕዝበ እግዚአብሔር ከመላው የሰው ልጅ ቤተሰብ ጋር አብሮ የሚጓዝበትን መንገድ ይመለከታል። ስለዚህ፣ እይታችን ከአማንያንና ከሌሎች ሃይማኖቶች ጋር ሊደረጉ በሚችሉ የጋራ ዕቅዶች፣ ከእምነት በራቁ ሰዎች፣ ከልዩ ማህበራዊ አካባቢና ቡድኖች እንዲሁም ከተቋሞቻቸው (የፖለቲካ፣ የባህል፣ የኢኮኖሚ፣ የፋይናንስ፣ የሠራተኛ፣ የሠራተኛ ማህበራት እና የንግድ ማህበራት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑና የሲቪል ማህበራት፣ ሕዝባዊ ንቅናቄዎች፣ የተለያዩ አናሳዎች፣ ድሆችና የተገለሉ ሰዎች) ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶችና ውይይቶች ላይ ማተኮር ይኖርበታል።

30. ተሞክሮዎችን ለማጉላትና ለውይይቱ አስተዋጽኦ ለማድረግ፣ «የገቢራዊ ሲኖዶሳዊነትን» የተለያዩ ገጽታዎች የሚገልጹ አስር ቁልፍ ርእሰ ጉዳዮችን ከዚህ በታች እናቀርባለን። እነዚህን ቁልፍ ርእሰ ጉዳዮች፣ ለመሳተፍና ምላሽ ለመስጠት ለሚቸገሩት ልዩ ትኩረት በመስጠት፣ በየጊዜው ከልዩ ልዩ አካባቢያዊ ሁኔታዎች ጋር ማጣጣም፣ ማቀናጀት፣ ማብራራት፣ አቅልሎ ማቅረብና ማዳበር ያስፈልጋል። ከዚህ የዝግጅት ሰነድ ጋር በተጓዳኝ የቀረበው መምሪያ ጸሎትን፣ ሕንጸትን፣ አስተንትኖንና የሐሳብ ልውውጥን በተጨባጭ ሊያነቃቁ የሚችሉ የተለያዩ ጥያቄዎችን ከመያዙም በላይ፣ ተፈላጊ ዘዴዎችን፣ ዝርዝር መግለጫዎችንና ምክረ ሐሳቦችን ያቀርባል።

I.

## 1. አብሮ ተጓዦች

በቤተክርስቲያንና በህብረተሰብ ውስጥ ሆነን በተመሳሳይ መንገድ ላይ ጎን ለጎን እንጓዛለን። በእናንተ የአጥቢያ ቤተክርስቲያን ውስጥ «አብሮ ተጓዦች» እነማን ናቸው? «ቤተክርስቲያናችን» ስንል የዚሁ ቤተክርስቲያን አካል ማነው? አብረን እንጓዝ ብሎ የሚጠይቀን ማነው? የመንገድ ጓደኞች፣ ከቤተክርስቲያን ውጭ ያሉት ጭምር፣ እነማን ናቸው? በሐሳብም ሆነ በተግባር ወደ ጎን የተገፉ ሰዎች ወይም ቡድኖች እነማን ናቸው?

II.

## 2. ማዳመጥ

ማዳመጥ ቀዳሚ እርምጃ ቢሆንም፣ አንዳች ጭፍን ጥላቻ የሌለበት ክፍት አእምሮና ክፍት ልብ ያስፈልጋል። ልዩ ቤተክርስቲያናችን ማንን «መስማት ያስፈልጋታል»? ምእመናን፣ በተለይም ወጣቶችና ሴቶች፣ የሚደመጡት እንዴት ነው? የወንድና ሴት ደናግላንን አስተዋጽኦ እንዴት እናቀናጃለን? የአናሳዎች፣ የተገለሉና የግፉአን ድምፅ የሚሰማበት ሁኔታ አለ? እንዳናዳምጥ የሚከለክሉንን ጭፍን ጥላቻዎችና ግትር ሐሳቦች ለይተን እናውቃቸዋለን? የምንኖርበትን ማህበራዊና ባህላዊ ሁኔታ የምናዳምጠው እንዴት ነው?

III.

### 3. መናገር

ሁሉም ሰው ነጻነትን፣ እውነትንና ፍቅርን በማጣመር በድፍረትና ያለ አንዳች ይሉኝታ መናገር ይጠበቅበታል። በማህበረሰብና በድርጅቶቹ ውስጥ ያለ ሸንገላና አድርባይነት ነጻና እውነተኛ የተግባቦት ስልት እንዴት እናዳብራለን? በህብረተሰብ ውስጥ ያለን የግንኙነት ዐይነት ምንድነው? ለእኛ የሚጠቅመንን ነገር የምንናገረው መቼና እንዴት ነው? ከካቶሊካዊ መገናኛ ብዙሃን በተጨማሪ ከሌሎች መገናኛ ብዙሃን ጋር ያለን ግንኙነት ምን ይመስላል? በክርስቲያን ማህበረሰብ ስም የሚናገረው ማነው፣ ተናጋሪዎቹስ የሚመረጡት እንዴት ነው?

IV.

### 4. ማክበር

«አብሮ መጓዝ» የሚቻለው ቃለ እግዚአብሔርን በጋራ በማዳመጥና መሥዋዕተ ቅዳሴን በማክበር ላይ የተመሠረተ ሲሆን ነው። ጸሎትና ሥርዓተ አምልኮ «የአብሮነት ጉዞአችንን» የሚያነቃቃውና የሚመራው እንዴት ነው? አስፈላጊ ውሳኔዎችንስ የሚያበረታታው እንዴት ነው? በሥርዓተ አምልኮና በሚቀድስ ሥራ የምእመናንን ሁሉ ንቁ ተሳትፎ የምናዳብረው እንዴት ነው? ለአንባቢና ለአገልጋይ የተሰጠ የአገልግሎት ቦታ ምንድነው?

V.

### 5. በተልእኮ ውስጥ ያለው የጋራ ኃላፊነት

ሲኖዶሳዊነት ሁሉም አባላት የሚሳተፉበት የቤተክርስቲያን ተልእኮ አስቻይ ሁኔታ ነው። ሁላችንም የወንጌል ልኡካን እንደመሆናችን መጠን፣ እያንዳንዱ የተጠመቀ ሰው የተልእኮው ተጋሪ የሚሆነው እንዴት ነው? ማህበረሰቡ  በማህበራዊና ፖለቲካዊ፣ በሳይንሳዊ ምርምርና በትምህርት፣ ማህበራዊ ፍትህን በማዳበር፣ ሰብአዊ መብቶችን በማስከበር እና የጋራ ቤትን በመንከባከብ ወዘተ. ረገድ ህብረተሰቡን በቁርጠኝነት እንዲያገለግል የሚያበረታታው እንዴት ነው? ሰዎች በተልእኮ አስተሳሰብ እነዚህን ግዴታዎች እንዲወጡ እንዴት ይረዳቸዋል? ከተልእኮ ጋር የተያያዙ ውሳኔዎችን ለይቶ ማወቅ የሚቻለው እንዴት ነው? በዚህ ሂደት የሚሳተፈውስ ማነው? የብዙ አብያተ ክርስቲያናት በተለይም፣ የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት፣ ቅርስ የሆኑ የተለያዩ ትውፊቶች፣ ከሲኖዶሳዊ ዘይቤ፣ ከውጤታማ ክርስቲያናዊ ምስክርነት አኳያ የተቀናጁትና  ከሁኔታዎች ጋር እንዲስማሙ የተደረጉት እንዴት ነው? የተለያዩ ራሳቸውን የቻሉ አብያተ ክርስቲያናት ባሉባቸው አካባቢዎች የትብብር ሁኔታ ምን ይመስላል?

VI.

## 6 . ውይይት በቤተ ክርስቲያንና በህብረተሰብ ውስጥ

ውይይት ጸጥታንና ሕመምን የሚያካትት፣ የሰዎችንና የሕዝቦችን ልምድ የማሰባሰብ ኃይል ያለው የጽናት መንገድ ነው። በልዩ ቤተክርስቲያናችን ውስጥ የሚገኙ የውይይት ቦታዎችና ዘይቤዎች ምንድን ናቸው? የራእይ ልዩነቶች፣ ግጭቶችና ችግሮች የሚፈቱት እንዴት ነው? በአቅራቢያ ባሉ ሰበካዎች፣ በአካባቢ በሚገኙ መንፈሳዊ ማህበራት፣ በምእመናን ማህበራትና ንቅናቄዎች ወዘተ. መካከል ትብብርን የምናዳብረው እንዴት ነው? ከሌሎች ሃይማኖቶች ተከታዮችና ከማያምኑ ወገኖች ጋር ምን ዐይነት የውይይት ተሞክሮዎችና የጋራ ጉዳዮች አሉን? ቤተክርስቲያን ከሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች፣ ከፖለቲካ፣ ከኢኮኖሚ፣ ከባህል፣ ከሲቪል ማህበራት፣ ከድሆች ወዘተ ጋር የምትወያየውና ከእነርሱም የምትማረው እንዴት ነው?

VII.

## 7 . ከሌሎች ክርስቲያን ቤተ እምነቶች ጋር

በአንዲት ጥምቀት በተሳሰሩ በተለያዩ ቤተ እምነቶች መካከል የሚደረገው ውይይት በሲኖዶሳዊ ጉዞ ውስጥ ልዩ ስፍራ አለው። ከሌሎች ክርስቲያን ቤተ እምነት ወንድሞችና እህቶች ጋር ያሉን ግንኙነቶች ምንድን ናቸው? የሚያሳስቡ ጉዳዮችስ ምንድን ናቸው? ከዚህ ‹‹የአብሮነት ጉዞ›› ያገኘናቸው ጥቅሞች ምንድን ናቸው? ችግሮቹስ ምንድን ናቸው?

VIII

## 8 . ሥልጣንና ተሳትፎ

ሲኖዶሳዊት ቤተክርስቲያን አሳታፊና የጋራ ኃላፊነት ያለባት ቤተክርስቲያን ናት። የምንከተላቸውን ግቦች፣ እነዚህንም ግቦች የምናሳካባቸውን መንገዶችና መወሰድ የሚገባቸውን እርምጃዎች የምንለየው እንዴት ነው? በልዩ ቤተክርስቲያናችን ውስጥ ሥልጣን እንዴት ተግባራዊ ይደረጋል? የቡድን ሥራና የጋራ ኃላፊነት ተሞክሮዎች ምንድን ናቸው? የምእመናን አገልግሎቶችና ኃላፊነትን የመሸከም ሥራ የሚበረታታው እንዴት ነው? ሲኖዶሳዊ አካላት በልዩ ቤተክርስቲያን ደረጃ ሥራቸውን የሚሠሩት እንዴት ነው? ሥራቸውስ ውጤታማ ነው?

IX.

## ፱. ማስተዋልና መወሰን

በሲኖዶሳዊ ዘይቤ፣ ውሳኔዎች የሚደረጉት በማስተዋል፣ ለመንፈስ ቅዱስ ካለ የጋራ ታዛዥነት በሚመነጭ የጋራ ስምምነት ነው። አንድን ነገር በጋራ ማስተዋልና ውሳኔ ማሳለፍ የሚቻልባቸው ሥርዓቶችና ዘዴዎች ምንድን ናቸው? የሥልጣን ተዋረድ ባላቸው ማህበረሰቦች ውስጥ በሚደረግ ውሳኔ አሰጣጥ ተሳትፎን ማዳበር የሚቻለው እንዴት ነው? የውይይት ምዕራፍን ከምክክር፣ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደትን ከውሳኔ መስጠት ወቅት ጋር አዛምደን የምንገልጸው እንዴት ነው? ግልጽነትንና ተጠያቂነትን የምናጠናክረው እንዴትና በምን ዘዴዎች ነው?

X.

## 10. በሲኖዶሳዊነት ራሳችንን ማነጽ

የአብሮነት ጉዞ መንፈሳዊነት ሰውን፣ ክርስቲያንን፣ ቤተሰቦችንና ማህበረሰቦችን ለማነጽ ዐይነተኛ ትምህርታዊ መርሆ ሊሆን ይገባል። ሰዎች፣ በተለይም በክርስቲያን ማህበረሰብ ውስጥ የኃላፊነት ሚና ያላቸው ሰዎች፣ «የአብሮነት ጉዞን» እንዲያዳብሩ፣ እርስ በርስ እንዲደማመጡና እንዲወያዩ አድርገን ማነጽ የምንችለው እንዴት ነው? ነገሮችን በማስተዋል እንዲለዩና ሥልጣናቸውን በአግባቡ እንዲጠቀሙ ምን ዐይነት ሕንጸት ልንሰጣቸው እንችላለን? ያለንበትን ባህልና እርሱም በቤተክርስቲያናችን ዘይቤ ላይ ያለውን ተጽእኖ ለመፈተሽ የሚረዱን ዘዴዎች ምንድን ናቸው?

# ለምክክር አስተዋጽኦ ማድረግ

31. የሲኖዶሳዊ ጉዞ የመጀመሪያ ምዕራፍ ዓላማ ከተለያዩ መገለጫዎቹና መልኮቹ፣ እንዲሁም ከየአካባቢው ተጨባጭ እውነታዎች ጋር የሚጣጣሙ ተገቢ ዘዴዎችን በመጠቀም፣ በሁሉም የተለያዩ ደረጃዎች የልዩ አብያተ ክርስቲያናትን መንፈሳዊ እረኞችና ምእመናንን በማካተት የገቢራዊ ሲኖዶሳዊነትን የካበቱ ልምዶች ለመቀመር ነው። በጳጳሳት የሚቀናጀው የምክክር ሐሳብ የሚቀርበው ‹‹ ለካህናት፣ ለዲያቆናትና ለቤተክርስቲያኖቻቸው ምእመናን፣ በግልም በማህበርም፣ እንዲሁም የወንድና ሴት ደናግላንን ጠቃሚ አስተዋጽኦ ባለመዘንጋት ይሆናል›› (EC, ቁ.7)። የልዩ አብያተ ክርስቲያናት ተሳታፊ አካላትን፣ በተለይም ‹‹ሲኖዶሳዊት ቤተ ክርስቲያን በእርግጥ የምትታነጽበትን›› (22) የካህናት ምክር ቤትንና የሐዋርያዊ ምክር ቤትን አስተዋጽኦ መጠየቅ ያስፈልጋል። ከዚህ ሌላ፣ የዝግጅት ሰነዱ የሚላክላቸው የሌሎች የቤተክርስቲያን አካላት እንዲሁም አስተዋጽኦዋቸውን በቀጥታ ለመላክ የሚፈልጉ ወገኖች ሐሳብ ጠቃሚ ይሆናል። በመጨረሻም፣ በልዩ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ሚና ወይም ኃላፊነት ያላቸው ወገኖች ብቻ ሳይሆን፣ የድሆችና የተገለሉ ሰዎች ድምፅም ቦታ እንዲያገኝ ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነው።

[22] ፍራንሲስኮስ፣ የጳጳሳት ሲኖዶስ የተመሠረተበት 50ኛ ዓመት መታሰቢያ ክብረ በዓል ሲከበር የተደረገ ንግግር

32. ከዚህ የማስተዋልና የማዳመጥ ሥራ በኋላ እያንዳንዱ ልዩ ቤተክርስቲያን የሚያቀርበው የተጠቃለለ ማብራሪያ ለኩላዊት ቤተክርስቲያን ጉዞ የራሱ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። ቀጣዮቹን የጉዞ ምዕራፎች ቀላልና ቀጣይ ለማድረግ፣ የጸሎትና የአስተንትኖ ፍሬዎችን ቢበዛ በአስር ገጾች ማጠቃለል ያስፈልጋል። እነርሱንም ፈር ማስያዝና በተሻለ ሁኔታ ማብራራት ካስፈለገ፣ እነርሱን የሚደግፉ ወይም የሚያጣምሩ ሌሎች ጽሑፎችን ማያያዝ ይቻላል። የሲኖዶሱ ብሎም የምክክሩ ዓላማ ፣ ሰነዶችን ለመቀመር ሳይሆን፣ «ህልሞችን ለመትከል፣ ከትንቢቶችና ከራእዮች ለመማር፣ ተስፋን ለማለምለም፣ መተማመንን ለመቀስቀስ፣ ቁስሎችን ለመጠገን፣ ግንኙነቶችን ለማቀናበር፣ የተስፋ ወጋገን እንዲበራ ለማድረግ፣ ከእርስ በርስ ለመማርና አእምሮን የሚያበራ፣ ልብን የሚያሞቅና ለእጆቻችን ጥንካሬ የሚሰጥ ብሩህ አእምሮ ለመፍጠር ነው» (23)።

[23] ፍራንሲስኮስ፣ ስለ ወጣቶች በሚመከረው የጳጳሳት ሲኖዶስ መክፈቻ ላይ ያደረጉት ንግግር (እ.አ.አ. ጥቅምት 3 ቀን 2018)

. . . We recall that the purpose of the Synod, and therefore of this consultation, is not to produce documents, but "to plant dreams, draw forth prophecies and visions, allow hope to flourish, inspire trust, bind up wounds, weave together relationships, awaken a dawn of hope, learn from one another and create a bright resourcefulness that will enlighten minds, warm hearts, give strength to our hands . . .

© 2021 - Amministrazione del Patrimonio della Sede Apostolica e Libreria Editrice Vaticana
Città del Vaticano - All rights reserved International Copyright handled by Libreria Editrice Vaticana
00120 Città del Vaticano
Tel. 06 698.45780

E-mail: commerciale.lev@spc.va

www.libreriaeditricevaticana.va
www.vatican.va

Graphic Design Lamorfalab Studio Creativo
www.lamorfalab.com

ሲኖዶስ
2014
2016

ለሲኖዶሳዊት ቤተ ክርስቲያን

ኣብሮነት / ተሳትፎ / ተልእኮ

SYNODUS EPISCOPORUM

SYNOD OF BISHOPS